**የተከበሩ አቶ ያለው አባተ!**

**የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባኤ!**

**የተከበሩ አቶ ገዱ አንዳርጋቸው!**

**የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፕሬዚዳንት!**

**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት!**

**ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

1. በአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግስት አንቀፅ 116 (2) እና የዋና ኦዲተር መ/ቤት እንደገና ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 186/2003 አንቀፅ 6 እና አንቀፅ 10(2) ለመስሪያ ቤቱ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የተከናወኑ ተግባራትን የሚገልፅ ዓመታዊ አጭር ሪፖርት ዋና ኦዲተሩ ለተከበረው ም/ቤት እንደሚያቀርብ የተደነገገ በመሆኑና ይህን ሪፖርት ለማቅረብ ዕድሉን በማግኘቴ የተሰማኝን ልባዊ ደስታ እየገለፅኩ የ2007 በጀት ዓመት የ11 ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ዓመታዊ አጭር ሪፖርት አቀርባለሁ፡፡
2. በዚህ አጭር ሪፖርት የዋና ኦዲተር መ/ቤት የ2007 በጀት ዓመት የ11 ወራት የዕቅድ አፈፃፀም አጭር ሪፖርት፣ መ/ቤታችን በ2006/2007 በጀት ዓመት ያከናወነው የ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት እና የክልሉ መንግስት የ2005 በጀት ዓመት የተጠቃለለ ፈንድ ሒሳብ ኦዲት ውጤትና ዋና ዋና ግኝቶች የያዘ አጭር ሪፖርት በቀደም ተከተል ቀርበዋል፡፡
3. ከዚህ በላይ በተናጠል የተመላከቱ ሪፖርቶችና ይህ የተጠቃለለ አጭር ሪፖርት በየደረጃው ለሚመለከታቸው አካላት በተለይም ለክልሉ ም/ቤት አፈ-ጉባዔ፣ ለምክር ቤቱ የበጀትና የመንግስት ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ለርዕሰ-መስተዳድርና ክልል መስተዳድር ም/ቤት ፅ/ቤት እንዲደርሱ ተደርጓል፡፡ በተለይም የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ሪፖርቶችን ለኦዲት ተደራጊዎችና ተቆጣጣሪ አካላት፣ የክልሉ የተጠቃለለ ፈንድ ሒሳብ ኦዲት ሪፖርትን ደግሞ ለክልላችን ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮና ለገቢዎች ባለስልጣን በግኝቶች ላይ ተገቢውን ማስተካከያ እንዲያደርጉ ቀደም ሲል ባስተላለፍነው ዝርዝር ሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

**የ2007 በጀት ዓመት የ11 ወራት የዕቅድ አፈፃፀም፣**

**የቁልፍ ስትራቴጅው የኦዲት ልማት ሰራዊት ግንባታ አፈፃፀም፣**

4. የ2007 በጀት ዓመት የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን መጨረሻ እንደመሆኑ መጠን የኦዲት ልማት ሰራዊት ግንባታችን ከሌሎች አመታት ጠንከር ባለና በተደራጀ አግባብ አመራር እየተሰጠበት የዋና ተልዕኳችን ማስፈፀሚያ አድርጎ ለመጠቀም ርብርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም አግባብ የመንግስትና የህዝብ አቅምን በማቀናጀት የልማት አቅሞችን አመለካከት፣ እውቀትና ክህሎት፣

አደረጃጀትና አሰራር እንዲሁም ግብዓት ጠንካራና ደካማ ሁኔታዎች በመለየት በየደረጃው የመፈፀም አቅምን ለመገንባት ሰፊ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

5. የመ/ቤታችን ሲቪል ሰርቫንት በልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መንግስት ውስጥ የሚኖረውን ሚናና በሚፈፅማቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች ምንነት ላይ ግንዛቤያቸው እንዲሻሻል ጥረት ተደርጓል፡፡ የህዝብ አቅምን ለይቶ ወደስራ ከመግባት አንፃር የክልላችን የግል ሒሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች ማህበር፣ የአማራ ሴቶችና ወጣቶች ፌደሬሽንን በህዝብ ክንፍነት በመለየት የተቋማችን ተልዕኮ፣ ተግባርና ፋይዳ እንዲገነዘቡ የተለያዩ መድረኮችን በመፍጠር ስልጠናዎችን መስጠት ተችሏል፡፡ የባለድርሻ አካላትም በኦዲት ምንነትና ፋይዳ ላይ ግንዛቤ መያዝ እንዲችሉ መድረኮች ተመቻችተው ስልጠናዎችን መስጠት ተችሏል፡፡ ከዚህ አንፃርም የኦዲት ተደራጊ ተቋማት ስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች፣ በየደረጃው የሚገኙ ም/ቤቶች አፈ-ጉባዔዎችና ቋሚ ኮሚቴዎች በየአመቱ በሚካሄደው የፋይናንስ ግልፅ አሰራርና ተጠያቂነት መድረክ በመሳተፍ ግንዛቤ መያዝ ችለዋል፡፡ በተጨማሪም የክልላችን የተለያዩ ተቋማትና የብዙሃን መገናኛ ኤጀንሲ ጋዜጠኞች በኦዲት ምንነትና ፋይዳ እንዲሁም በኦዲት ሪፖርቶች አዘጋገብ ግንዛቤ መያዝ የሚያስችል ስልጠናዎችን መስጠት ተችሏል፡፡

6. ከክህሎት ግንባታ አንፃር በዋናነት ዓላማ ፈፃሚ ኦዲተሮችን ማዕከል ያደረገ ዓመታዊ የ40 ሰዓት የአቅም ግንባታ ስልጠና፣ የጀማሪ ኦዲተሮች የቅድመ ስራ ስልጠና ተሰጥተዋል፡፡ የ1ለ5 መድረኮችን የክህሎት ሽግግር ማስፈፀሚያ አድርጎ ለመጠቀም በየጊዜው የመወያያ ርዕሰ ጉዳዮች እየተመረጡ መማማር እንዲኖር ተደርጓል፡፡ ከአደረጃጀት አንፃርም በመ/ቤታችን የምስራቅ አማራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤትን ከማጠናከር ጎን ለጎን የመስክ ኦዲተሮችን ጨምሮ 69 የ1ለ5 አደረጃጀቶች ተፈጥረው ወደ ስር ተገብቷል፡፡ ከአሰራር አንፃርም የልዩ ኦዲት አስተዳደር መመሪያ ተቀርፆ ወደ ስራ የተገባ ሲሆን የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ማስተር ሊስት፣ የኦዲተሮች የተጠቃለለ የህግ ማዕቀፍ (compliance package) ተቀርፀው ወደ ስራ የተገባ ሲሆን የአፈፃፀም ግምገማና የግብረ-መልስ ስርዓትም ተጠናክሮ እየተፈጸመ ይገኛል፡፡ ከለውጥ ፕሮግራሞች መካከልም ለውጤት ተኮር ስርዓት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ይገኛል፡፡

7. በአጠቃላይ ከዚህ በላይ በተመላከቱ የኦዲት ልማት ሰራዊት ግንባታ ስራዎች የተገኙ ውጤቶችና አሁንም የሚቀሩ ደካማ ዝንባሌዎች ተለይተዋል፡፡ በውጤት ደረጃ የተገኙ ማሳያዎችን ለመጥቀስ ያክል፣ የመ/ቤታችን ሰራተኞች በኦዲት ሰራዊት ግንባታ ምንነትና ፋይዳ ያላቸው ግንዛቤ ጥሩ መሻሻል ማሳየቱ፣ሲቪል ሰርቫንቱ በልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መንግስት ውስጥ ስላለው ሚናና በፖሊሲዎቻችንና ስትራቴጅዎች ላይ ጥሩ ግንዛቤ መያዝ መቻሉ፣ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጅዎችን የስራ ዕቅዶች መነሻና የግብ ውጤቶች መለኪያ አድርጎ የመውሰድ ጅምር አበረታች መሆኑ፣ የህዝብ ጥቅምን ማስቀደምና መጠነኛ ቢሆንም ዕቅድን በታታሪነት ለመፈጸም ዝግጁነት እየታየ መምጣቱና አጭር ሊባል በሚችል ጊዜ ውስጥ ሰፊ ስራዎችን የማጠናቀቅ ልምድ እየዳበረ መምጣቱ፣ በኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር

ምንነት ላይ ሙሉ ግንዛቤ ተይዞ የዚሁ አመለካከትና ተግባር መደበቂያ በሆኑት የትምክህተኝነት፣ የጠባብነትና አክራሪነት አደጋዎች ላይ ትግል የማድረግ ጥሩ ጅምር መኖሩ፣ ኦዲተሮች የተለያዩ የኦዲት አይነቶችን የመፈጸም ክህሎታቸው አንፃራዊ መሻሻል ማሳየቱ፣ የኦዲት ሽፋናችን መሻሻል መቻሉና ኦዲቱን በዕቅድ ለመምራት እገዛ የሚያደርጉ አሰራሮች መዘርጋት መቻላቸው የተገኙ ውጤቶችና በጠንካራ አፈፃፀም ሊታዩ የሚችሉ ናቸው፡፡

8. የኦዲት ልማት ሰራዊቱ የተሟላ ቁመና ይዞ ከሒደቱ የተፈለገውን ውጤት ማምጣት እንዳንችል አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳደሩ በድክመት የተለዩ ተግዳሮቶችም አሉ፡፡ ይኸውም፣ የአመለካከት ግንባታ ስራዎችን ባልተገባ መንገድ ከመ/ቤቱ ሙያዊ ገለልተኝነት ጋር ማያያዝ በባለሙያዎች በኩል የሚታይ መሆኑ፣ በአንዳንዶች ላይ የታታሪነት መጓደልና የስነ-ምግባር ችግሮች መኖር፣ የተለያዩ ጥቅማጥቅም ፍለጋ መ/ቤቱን የመልቀቅ ችግር ሰፊ መሆኑ (በስትራቴጅክ ዘመኑ በየበጀት ዓመቱ በአማካኝ ከሚቀጠሩት 42 ኦዲተሮች መካከል 55% የሚሆኑት የሚለቁ መሆኑ)፣ መ/ቤታችንን ስህተት ፈላጊ አድርጎ የማየት አመለካከት ገና ሙሉ በሙሉ የተቀረፈ አለመሆን፣ ለኦዲት ሪፖርቶች ምላሽ የማይሰጡና እርምጃ አወሳሰዳቸው አዝጋሚ የሆነ ኦዲት ተደራጊዎች መኖራቸው፣ የተቀራረበ ክህሎት የመገንባት ስራው ገና የሚቀረው መሆኑ፣ የጥራት ጉድለት የሚታይባቸው አንዳንድ የኦዲት ሪፖርቶች መኖራቸው፣ የ1ለ5 አደረጃጀትን በሳል ውይይት የሚካሄድባቸው መድረኮች አድርጎ ያለመጠቀም፣ የውጤት ተኮር ስርዓቱን ውጤታማ በሆነ መልኩ አለመፈጸምና ዘመናዊ ቴክኖሎጅዎችን የሚጠቀም የኦዲት ስርዓት በመገንባት በኩል ስራው ጅምር መሆኑና ከግብዓት አንጻርም ለመስክ ክትትልና ድጋፍ የሚሆን በቂ ተሽከርካሪ አለመኖር የሚሉት በውስንነት የሚታዩ ናቸው፡፡

9. በአጠቃላይ ከዚህ በላይ በየአቅም ግንባታ ስትራቴጅዎች በጥንካሬና በድክመት በጥልቀት የቀረቡ ግምገማዎች ሲታዩ የቁልፍ ተግባሩን ለማሳካት የተደረገው ርብርብ መ/ቤታችን በትክክለኛ የትኩረት መስመር ላይ መሆኑ እንዳለ ሆኖ፣ በአመራሩ፣ በሲቪል ሰርቫንቱና በህዝብ ክንፎቻችን መካከል የተቀራረበ የአመለካከት አንድነት ለመፍጠር የተደረገው ትግል የፈጠራቸው ምቹ ሁኔታዎች እንዳሉ ሆነው አሁንም ቀጣይ ስራ የሚጠይቅ መሆኑ፣ በፈፃሚ ባለሙያዎችና ቡድኖች መካከል የተቀራረበ ክህሎት ለመፍጠር የተደረገው ጥረት ለመነሻ የሚሆኑ ውጤቶችን ከማሳየቱ በስተቀር አሁንም የርብርብ ማዕከል መሆን ስለሚገባው፣በአጠቃላይ ውጤትም ሲታይ በስትራቴጅክ ዘመኑ መጨረሻ 60% የሚሆኑትን ሲቪል ሰርቫንቶች ግምባር ቀደም ለማድረግ ታቅዶ ማሳካት የተቻለው 31.5% (ወ=55 ሴ=26 ድ=81) ያክሉን ብቻ መሆኑ፣ ከመ/ቤታችን ሰራተኞች መካከል በውጤት ተኮር ምዘናቸው ከፍተኛና ከዛ በላይ መሆን የቻሉት ከ10% የማይበልጡ መሆናቸውና የመ/ቤታችን የፊዚካል ስራዎች አፈፃፀም በመካከለኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑ ተዳምረው ሲታዩ በመ/ቤታችን የኦዲት ሰራዊት ለመገንባት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል ከማለት

በስተቀር የኦዲት ልማት ሰራዊት ተገንብቷል ማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም ይሄንኑ ቁልፍ ተግባር የማሳካት ጉዳይ የቀጣይ ስትራቴጅክ ዘመን ስራ ሆኖ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

**የመልካም አስተዳደር ስራዎች አፈፃፀም፤**

10. መ/ቤታችን በዋናነት የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ተቋማዊ በሆነ መልኩና በቀጣይነት መፍታት እንዲቻል የለውጥ ፕሮግራሞችን አጥብቆ ይዞ ብልሹ አሰራሮችን በመታገል የመፈፀም አቅሙ የጎለበተ ኦዲት ተቋም ለመፍጠር እየሰራ ነው፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎንም የኦዲት ተደራሽነት ጥያቄዎችን ምላሽ ለመስጠት ባለፉት አመታት የኦዲት አገልግሎት ሳያገኙ የቆዩ የክልላችን ወረዳዎች (ጠለምት፣ በየዳ፣ ጠገዴ፣ምዕራብ አርማጭሆ፣ሰሃላ ሰየምት፣ አበርገሌና በረኸት) ወረዳዎች የኦዲት አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል፤ ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸውን የከተሞች መሰረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም (ULGDP) ተጠቃሚ ከተሞች (ያለፉ ዓመታትን ሂሳብ ጨምሮ) ሂሳብ ኦዲት እና ለምዕተ-ዓመቱ የልማት ግቦች ማስፈፀሚያ የተመደበን (MDG) በጀት ራሱን አስችሎ ኦዲት በማድረግ የህዝብ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

**የህዝብ ግንኙነት ስራዎች አፈፃፀም፤**

11. የመ/ቤታችን የህዝብ ግንኙነት ስራዎች በአብዛኛው በአመለካከት ለውጥና በገፅታ ግንባታ ስራዎች ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው፡፡ በመሆኑም ከአመለካከት ለውጥ ጋር በተያያዘ በዚህ ሪፖርት በኦዲት ልማት ሰራዊት ግንባታ ስራዎች የተመላከቱ አፈፃፀሞች በአብዛኛው የህዝብ ግንኙነት ስራዎች ናቸው፡፡ ከዚህም በላይ የዋና ኦዲተር መ/ቤትን ገጽታ ለመገንባትና የመ/ቤታችንን አንኳር አፈፃፀሞች ለህዝብ እንዲደርሱ ለማድረግ የክልላችን ብዙሃን መገናኛ በስፋት የተጠቀምን ሲሆን የማህበራዊ ድህረ-ገፅም ባደገ ሁኔታ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የህትመት ውጤቶች ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እንዲደርሱ ከመደረጉም በላይ የመ/ቤታችን አፈፃፀም ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገርና ምርጥ ተሞክሮዎችን ለመቀመር ም/ቤታችን ባደረገልን ድጋፍ የውጭ ሐገርን ተሞክሮ ጭምር ለማየት ተችሏል፡፡

**የኦዲት ሥራ ዕቅድ አፈፃፀም፤**

**የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት አፈፃፀም፤**

12. መ/ቤታችን በ2007 በጀት ዓመት የ480 ኦዲት ተደራጊዎችን የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት በማከናዎን የኦዲት ሽፋንን ከመ/ቤት ቁጥር አንፃር 70%፣ ከበጀት አንፃር 75% እና በገቢ በጀት ደግሞ 30% ሽፋን ለማድረስ ታቅዶ ነበር፡፡ በተጨማሪም የክልሉን መንግስት የ2005 በጀት ዓመት የተጠቃለለ ፈንድ ሒሳብ ኦዲት ለማድረግ ዕቅድ ተይዞ ነበር፡፡

13. በበጀት ዓመቱ 11 ወር ውስጥ የ368 መ/ቤቶችን የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ማከናዎን በመቻሉ ከዕቅዱ አንፃር የ77% አፈፃፀም ያለው ሲሆን ይህ አፈፃፀም የኦዲት ሽፋናችንን በ2003 በጀት ዓመት ከነበረበት 23% ከእጥፍ በላይ በማሳደግ ከኦዲት ተደራጊዎች ቁጥር አንፃር ሽፋናችንን 54% ማድረስ አስችሏል፡፡ በዚህ በጀት ዓመት ኦዲት ከተደረጉት 368 መ/ቤቶች መካከል 8ቱ በግል በተፈቀደላቸው

ኦዲተሮች ኦዲት የተደረጉና የኦዲት ስራችን አካል ተደርገው የተወሰዱ ናቸው፡፡ የ2005 የክልሉን መንግስት የተጠቃለለ ፈንድ ሒሳብ ኦዲት በማድረግ ሪፖርቱ ወጪ የተደረገ ሲሆን በዚህ ዓመታዊ ሪፖርት በአጭሩ ለም/ቤቱ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ የኦዲት ሽፋኑ ከበጀት አንፃር ሲታይ አጠቃላይ ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች የበጀት ወጪ ብር 12,302,191,009 በመሆኑ ለ2006 በክልሉ ም/ቤት ከታወጀው ብር 18,753,855,437 አኳያ ሲታይ 65.6% የደረሰ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ የገቢ ኦዲት ሽፋን በበጀት ዓመቱ ማጠቃለያ ሪፖርት የሚታይ ሲሆን አፈፃፀሙም ከዕቅዳችን ጋር ተቀራራቢ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡ የኦዲት ሽፋናችንም በክልላችን ካሉ አጠቃላይ ኦዲት ተደራጊዎች አንፃር አፈፃፀሙ በሚፈለገው ደረጃ ላይ ደርሷል ባይባልም በሐገር አቀፍ ደረጃ የክልሎች ኦዲት ሽፋን በ2007 በጀት ዓመት በዝቅተኛው መመዘኛ (minimum audit coverage) 50% ማድረስ እንዲቻል የተጣለውን ሐገራዊ ግብ ማሳካት ተችሏል፡፡

**የክዋኔና አካባቢ ጥበቃ ኦዲት አፈፃፀም፤**

14. በበጀት ዓመቱ 12 የክዋኔ ኦዲቶችን (6 መደበኛ ኦዲቶችና 6 የክትትል ኦዲቶችን) በማከናዎን የአፈጻጸም ውጤታማነትን ለማረጋገጥና የአሰራር ማሻሻያዎችን ለማመላከት ዕቅድ ተይዞ ነበር፡፡ ይህ ሪፖርት እስከተጠቃለለበት ጊዜ ድረስ የ6 መደበኛ ክዋኔ ኦዲቶችንና የ5 ክትትል ኦዲቶችን መፈጸም በመቻሉ አፈፃፀሙ 92% ሲሆን የበጀት ዓመቱን ማጠቃለያ ጊዜ በመጠቀም ከአንድ ወር የማይበልጥ የዕቅድ ቆይታ ያላቸውን ቀሪ የክትትል ኦዲት ስራዎች በማጠናቀቅ እንደእቅዳችን ለመፈጸም ጥረት ላይ እንገኛለን፡፡

15. የክዋኔና የአካባቢ ጥበቃ ኦዲት የክልሉ መንግስት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ያስገኙት ውጤት ሕጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሰራር የተፈፀመ መሆኑንና ተፈላጊውን ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ የሚከናዎን ስለሆነ የኦዲት ተደራጊ አካላትን ትኩረት የሳበ በመሆኑ ራሱን በቻለ የስራ ሒደት እንዲደራጅ በስራ አመራሩ ስምምነት ተይዞ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት በመቅረፅ ለሚመለከተው በማቅረብ ወደ ስራ ለማስገባት ጥረት ቢደረግም ውሳኔ ባለማግኘቱ በበጀት ዓመቱ መፈጸም አልቻለም፡፡

**የሙያ ብቃት ማረጋገጥና ክትትልን በሚመለከት፤**

16. በአዋጅ ቁጥር 186/2003 አንቀፅ አንቀፅ 6(2) (ኀ) መሰረት መ/ቤታችን በክልሉ ውስጥ በኦዲት ሙያ ለሚሰሩ የግል ኦዲተሮችና የሒሳብ አዋቂዎች በስራው መስክ ለመሰማራት የሚያስችላቸውን የሙያ ብቃት የምስክር ወረቀት መስጠትና የክትትል ስራ ማከናዎን ከዓበይት ተግባሮቻችን መካከል አንደኛው ነው፡፡

17. እስከዚህ ሪፖርት ዝግጅት ድረስ በመ/ቤታችን ፈቃድ ወስደው በሙያው የተሰማሩ የግል ሒሳብ አዋቂዎች በድምሩ 309 (ወንድ 280 ሴት 29) እና የግል ኦዲተሮች በድምሩ 20 (ወንድ 18 ሴት 2) ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ በ2007 በጀት ዓመት ለ70 የግል ሒሳብ አዋቂዎች (ሴት 20) እና ለ5 የግል ኦዲተሮች (1 ሴት) አዲስ ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡ በበጀት ዓመቱ 266 ባለሙያዎች ፈቃዳቸውን አድሰዋል፡፡

የባለሙያዎችን ክትትልና ድጋፍ በሚመለከት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየሰራን ሲሆን በተለይም የግል ሒሳብ አዋቂዎች ከገቢዎች ባለስልጣን ጋር ቀጥተኛ የስራ ግንኙነት ስላላቸውና ጠንካራ ክትትል የሚደረግ በመሆኑ መረጃውን በመለዋወጥ የመደገፍና የማረም ስራ እየሰራን ነው፡፡ እነዚሁ የሂሳብ አዋቂዎችና የግል ኦዲተሮች በክልል አቀፍ የሙያ ማህበር እንዲደራጁ አስፈላጊው ድጋፍና እገዛ ተደርጎላቸው ህጋዊ ማህበራቸውን መስርተው እየተንቀሳቀሱ ሲሆን ሙያውን ለማሳደግና የሙያ ስነ-ምግባራቸውን ለማስጠበቅ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡

18. ይሁን እንጅ የፌደራል መንግስት የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር 847/2006 ያወጀና የኢትዮጵያን የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድን በሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 332/2007 ያቋቋመ በመሆኑና የክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤቶች አዋጁና ደንቡ ፀንቶ ወደ ስራ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ለግል ሒሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች ፈቃድ መስጠት እንድናቆም የኢፌዴሪ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በደብዳቤ ያሳወቀን በመሆኑ ከበጀት ዓመቱ ሦስተኛ ሩብ ዓመት ጀምሮ ፈቃድ መስጠት አቁመናል፡፡ ይህን ተግባር በአዋጅ የሰጠን የክልሉ ም/ቤት ከመሆኑ አንጻር ሁኔታውን ለክልላችን ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት በወቅቱ አሳውቀናል፡፡

**የሰው ሐይል አስተዳደርና ተያያዥ አፈፃፀሞች፤**

19. በዚህ በጀት ዓመት የምስራቅ አማራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤታችን ከተፈቀደለት የሰው ሀይል መዋቅር ውስጥ 76 (68%) የሚሆኑትን በማሟላት ወደ ስራ ገብቷል፡፡መ/ቤታችን ካለው አጠቃላይ 328 የስራ መደብ መዋቅር ውስጥ 281 (85.6%) የሚሆኑት (62.2% አላማ ፈፃሚና 23.4% ድጋፍ ሰጪ) በሰው ሃይል የተሟሉ ናቸው፡፡ ከተሟላው የሰው ሃይል መዋቅር ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ 22.7% ሲሆን ከዚሁ ድርሻ አላማ ፈፃሚዎች 10.6% እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች 12.1% ናቸው፡፡ ከዕድሜና ከትምህርት ዝግጅት አንፃር የሰው ሃይላችን ሲታይ 76% ሰራተኞች ዲግሪና ከዛ በላይ የትምህርት ዝግጅት ያላቸው ሆኖ 53% ሰራተኞች ደግሞ ወጣቶች ናቸው፡፡

20. ከሰው ሀይል አስተዳደር አንፃር መ/ቤታችን የገጠመው ፈታኝ ችግር ልምድ ያላቸው ከፍተኛና የቡድን ኃላፊ ደረጃ ያላቸው ኦዲተሮች የተሻለ ክፍያና ጥቅማጥቅም ፍለጋ እየለቀቁ መሆናቸውና በኦዲት ጥራት ስራችን ላይ ከፍተኛ ችግር እየገጠመን መሆኑ ነው፡፡በመሆኑም የመ/ቤታችን የእስከአሁን ጥሩ የመፈጸም ብቃትና የኦዲት ጥራት ለማስቀጠል ም/ቤቱ ለችግሩ ተገቢውን መፍትሄ ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡

**የበጀት አፈፃፀምና አጠቃቀም፤**

21. መ/ቤታችን ለበጀት አመቱ የተስተካከለ ብር 27,315,644.00 (ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ብር 7,325,887.00) መደበኛ በጀት ተፈቅዶለታል፡፡ በተጨማሪም ከመሰረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ ፕሮግራም(Promotion of Basic Services III) ብር 2,316,186.00 ከልማት አጋሮች በተጨማሪ በጀትነት ተመድቦለታል፡፡የመደበኛ በጀቱ የ11 ወር አፈፃፀም ሲታይ ቅድሚያ ክፍያዎችንና ግዴታ የተገባቸው ወጪዎችን ጨምሮ 89%

ነው፡፡የመሰረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ ፕሮግራም በጀት ተመሳሳይ ወቅት አፈፃፀም ደግሞ 92.7% ነው፡፡ የአመቱ ማጠቃለያ በጀት አፈፃፀማችን አሁን ካለው አፈፃፀም መሻሻል እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡

22. የበጀት አስተዳደርና አጠቃቀምን በሚመለከት በየጊዜው በተጠናከረ የውስጥ ኦዲት ስርዓት በመታገዝ በውስጥ ኦዲቱ በኩል የሚቀርቡ ጥቃቅን የግኝቶችና የአሰራር ግድፈቶች በየጊዜው ትኩረት ሰጥቶ በማሻሻል የክልሉ መንግስት የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ህጎች መሰረት በማድረግ ለመምራት ጥረት ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጅ የበጀት አመቱ ሒሳብ ምክር ቤት በሚሰይመው ገልለተኛ ኦዲተር ያልተረጋገጠ በመሆኑ ወደፊት ም/ቤቱ በየጊዜው ገለልተኛ ኦዲተር እየሰየመ ኦዲት ማስደረግ የሚገባው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የ2006 እና የ2007 በጀት አመት ሒሳብ በዚህ ክረምት በመ/ቤታችን የውጭ ኦዲተሮች ተመርምሮ ሪፖርቱ ለመ/ቤቱ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡

**የተከበሩ አፈ-ጉባዔ!**

**የተከበሩ ፕሬዚደንት!**

**የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

**የክልሉን መንግስት የ2005 በጀት ዓመት ዓመታዊ የተጠቃለለ ፈንድ ሂሣብ ኦዲት ውጤት ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡**

**ለመደበኛ በጀት የባንክ ሒሳብ ማስታረቂያ ያልተዘጋጀለት መሆኑ፤**

23. በክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የሚንቀሳቀሰው የክልሉ የትሬዠሪ ሂሣብ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ጀኦቪ-116 በበጀት ዓመቱ ከባንክ የተገኘው የባንክ ሂሳብ ማስታወቂያ (bank statement) የሚያሳየው ከወጪ ቀሪ በቢሮው ከሚዘጋጀው የባንክ ሂሳብ መከታተያ ሌጀር ጋር በማነፃፀር ልዩነት ላለመኖሩ ለማረጋገጥ የሚያስችል የባንክ ሂሳብ ማስታረቅ (bank reconcilation) ስራ ያልተሰራና መግለጫም ያልተዘጋጀለት መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም በባንክ የተንቀሳቀሰውና ከወጪ ቀሪ ሆኖ የሚታየው የክልሉ የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ ትክክለኛና አንዳች ችግር ያልተከሰተበት ስለመሆኑ በኦዲት ማረጋገጥ እንዲቻል ለዚሁ ተግባር ተገቢው ባለሙያ ተመድቦ ከስር ከስር ከባንክ ጋር እተናበበ ልዩነት ሲከሰትም እየታረቀ የሂሳብ እንቅስቃሴው ደህንነት እንዲጠበቅና መግለጫውም ተዘጋጅቶ ለኦዲት መቅረብ እንዳለበት በኦዲት ሪፖርታችን አስተያየት የሰጠን ሲሆን ቢሮው በሰጠው ግብረ መልስ ባለሙያዎች ተከፋፍለው እየሰሩ ቢሆንም ስራውን ለማጠናቀቅ ከመደበኛ ስራ ጋር ተጨማሪ የሰው ሃይልና ጊዜ በመጠየቁ ምክንያት በኦዲት ወቅት አጠናቆ ለማቅረብ ስላልተቻለ ለተግባሩ ተጨማሪ የስራ መደብ ለማስፈቀድ ጥረት እያደረገ መሆኑን ገልጧል፡፡

**የገቢ ሒሳብ ዕቅድ ክንውን በሚመለከት፤**

24. ለ2005 በጀት ዓመት የታወጀው የተስተካከለ የገቢ እቅድ ብር 17,060,779,476 ሲሆን በቀረበው የሂሳብ መግለጫ መሰረት ብር 16,296,226,221.21 (95.5%) የተሰበሰበ ሲሆን የተሰበሰበው ከታቀደው የገቢ ዕቅድ ጋር ሲነፃፀር ከመደበኛ ገቢ ብር 332,009,714.02 (8.3%) እና ከምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ በጀት (MDG) ብር 598,894,114.00 (12.9%) ከታቀደው በታች የተሰበሰበ ሲሆን በሌላ በኩል ግን ከእርዳታና ብድር ብር 166,350,573.23 (77.63%) ይሰበሰባል ተብሎ ከታቀደው በጀት በላይ የተሰበሰበ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

25. በአጠቃላይ የበጀት አመቱ ገቢ ከእቅዱ ጋር ሲነጻጸር የሚታየው ልዩነት ዋነኛው ምክንያት ከፌደራል መንግስት ይገኛል ተብሎ የታቀደው የምዕተ ዓመቱ ግቦች ማስፈፀሚያ በጀት (MDG) እና ከታክስ፤ከካፒታል ዋጋ እድገት፤ከከተሞችና ሌሎች ገቢዎቸ ይሰበሰባል ተብሎ ከታቀደው በታች አፈፃፀም በመኖሩ መሆኑ ታውቋል፡፡ ስለሆነም የገቢ አሰባሰባቸው ከእቅድ በታች ለሆኑት የከተሞችን

ገቢ የመሰብሰብ አቅም በማጎልበት የታቀደውን አሚጦ በመሰብሰብ በመንግስት የተያዘውን ልማት ለማሳካት የሚደረገው ጥረት በሚገባ መደገፍና የክልሉን ወጪ በራሱ የመሸፈን አቅም ይበልጥ ማጠናከር ይገባል የሚል አስተያየት የተሰጠ ሲሆን ቢሮው ስለሁኔታው በሰጠው ግብረ መልስ እንዳስታወቀው ክልሉ ከፌደራል መንግስት የሚጠበቀው ድጎማ (MDG) በጀት እንዲለቀቅ የተቻለውን ጥረት ቢያደርግም ከፌደራል መንግስት የታቀደውን ያህል ባለመለቀቁ ምክንያት መሆኑን ገልጾ ከእቅድ አንጻር ለታዩ ክፍተቶች ወደፊት ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር በመመካከር በተሻለ ሁኔታ አቅዶ ለመሰብሰብ ጥረት የሚደረግ መሆኑን ገልጧል፡፡

**በወቅቱ ያልተወራረደ የተሰብሳቢ ሒሳብ ኦዲትን በሚመለከት፤**

26. ሰኔ 30/2005 ዓ.ም ላይ በክምችት የተገኘው የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 5,074,980,338.53 ሲሆን በእድሜ ተተንትኖ ያልተያዘ በመሆኑ ምን ያህሉ መጠን ለምን ያህል የጊዜ ቆይታ እንዳለው ማረጋገጥ ባይቻልም በ2004 በጀት ዓመት ከነበረው ጠቅላላ የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 4,140,475,567.87 ጋር ሲነፃፀር የ2005 በጀት ዓመት በብር 939,504,770.66 (22.57%) ጭማሪ ያለው ሲሆን ለጭማሬው ዋናው ምክንያት በ2005 በጀት ዓመት የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ማስፈፀሚያ በጀት (MDG) በ6 ፈጻሚ ቢሮዎች በተሰብሳቢ ሂሳብ የተያዘ ብር 606,389,274.16 ከጭማሬው 64.9% ድርሻ የያዘ መሆኑ ታውቋል፡፡ በመሆኑም ሂሳቡን በማጣራት በሚደረስበት ውጤት መሰረት በዕድሜ ተተንትኖ እንዲያዝ ተደርጎ መሰብሰብ/መወራረድ የሚችለውን ሂሳብ እንዲሰበሰብ/እንዲወራረድ ይህን ማድረግ ያልተቻለው ደግሞ ምክንያቱ እየተጣራ በስራ ላይ ባለው የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 6/2004 አንቀፅ 14 /1-5 መሰረት ከመዝገብ እንደሰረዝ ለእያንዳንዱ መ/ቤት አቅጣጫ እንዲሰጥበት የኦዲት አስተያየት ተሰጥቶ ቢሮው በክልል ሴክተር መ/ቤቶች፤በዞኖች፤በወረዳዎችና በከተማ አስተዳደሮች አጣሪ ኮሚቴ ተቋቁሞ በእድሜ እየተተነተነ መሰብሰብ የሚችለውና የማይችለውን የማጣራት ስራ በመሰራት ላይ መሆኑን ከሰጠው ግብረ መልስ መገንዘብ ተችሏል፡፡

**የተከፋይ (ዕዳ) ሒሳብ ኦዲትን በሚመለከት፤**

27. ሰኔ 30/2005 ዓ.ም ላይ በክልሉ ውስጥ ብር 2,755,833,062.15 የተከፋይ ሂሳብ በእድሜ ሳይተነተን የተገኘ ሲሆን ይኸው ከ2004 በጀት ዓመት ብር 2,223,364930.88 ጋር ሲነፃፀር የ2005 በጀት ዓመት በብር 532,468,131.27 (23.95%) ጭማሪ ያለው መሆኑ ታውቋል፡፡ ከዚህ ውስጥ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ማስፈጸሚያ በጀት (MDG) ተከፋይ ሂሳብ ብር 102,821,856.35 ከጭማሬው 19.31% የሚይዝ ሲሆን ሌሎች በተከፋይ ከሚታዩ ሂሳቦች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የደመወዝ ተከፋይ፤የጡረታ ተከፋይ፤ሌሎች የደመወዝ ተቀናናሾች፤የንግድ ስራ ትርፍ ግብር፤የተጨማሪ እሴት ታክስ ተከፋይ ሂሳቦች ለሚመለከታቸው በወቅቱ ባለመተላለፉ እንዲሁም የባንክ ቁጥራቸው ‹ቢ› በሆኑ የባንክ ሂሳቦች የነበረውን የበጀት ዓመቱ ተራፊ በጀት ከወጪ ቀሪ ሰኔ 30/2004 ብሎክ በማድረግ ወደ ትሬዠሪው ፈሰስ

በተደረገበት ወቅት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ለሴክተሮች ተከፋይ በማለት በ5028 በተከፋይ ሂሳብ መያዙ ለጭማሪው አስተዋፅኦ የነበረው መሆኑ ታውቋል፡፡ በክልሉ የተከማቸውን የተከፋይ ሂሳብ በማጥራትና በመክፈል የራሱን የተጣራ ሀብት ለይቶ በማወቅ በተጣራ ሀብቱ ላይ ወቅታዊ ውሳኔ ማሳለፍ እንዲችል በሪፖርት ላይ የታየው የተከፋይ ሂሳብ ሊከፈል የሚችለው እየተለየ ለሚመለከተው አካል መከፈል እንዳለበት አስተያየት ተሰጥቶ ቢሮው የተከፋይ ሂሳብን እንደ ተሰብሳቢ ሂሳብ ሁሉ አጣሪ ኮሚቴ ተቋቁሞ የእድሜ ትንተናና የማጣራት ስራ እየተሰራና እየተወራረደ በየሩብ ዓመቱ ሪፖርት እንዲቀርብ መመሪያ ያስተላለፈና እየተከታተለ መሆኑን በመግለጽ ምለሽ ሰጥቷል፡፡

**በኦዲት አስተያየት መሰረት የተስተካከለ ሂሳብ መግለጫ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ማቅረብን በሚመለከት፤**

28. በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003 አንቀፅ 55/2 መሰረት ቢሮው ከመንግስት መ/ቤቶች የሚደርሰውን የተመረመረ የሂሳብ ሪፖርት በማጠቃለል የክልሉ መንግስትን አመታዊ የሂሳብ ሪፖርት ማዘጋጀት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ሪፖርት አቅራቢ መ/ቤቶች በዋና ኦዲተር መ/ቤት በተሰጣቸው የኦዲት አስተያየት መሰረት የተስተካከለ ሂሳብ መግለጫ እያቀረቡ ይኸው ሊጠቃለል ሲገባ በናሙና በተመረጡ ሪፖርት አቅራቢ መ/ቤቶች እንደተረጋገጠው አስቀድሞ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የሂሳብ መግለጫው ሳይስተካከል ከኦዲት በፊት በነበረበት ሁኔታ (ያልተስተካከለ) የሂሳብ መግለጫ በማቅረብ በክልሉ የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ ውስጥ የተካተተበት ሁኔታ መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡በዚህ ሁኔታ ጉልህ የሆኑ የኦዲት ግኝቶች ሳይስተካከሉ የተሳሳተ ሪፖርት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮው የሚያቀርቡ ከሆነና ይኸው ከነስህተቱ በክልሉ የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ ውስጥ ሲካተተ የክልሉ የተጠቃለለ ፈንድ ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ ከማድረጉም በተጨማሪ በዚህ ላይ ተመስርቶ ውሳኔ ማሳለፍ ስህተት ላይ የሚጥል በመሆኑ እያንዳንዱ ሪፖርት አቅራቢ በተሠጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ሂሳብ መግለጫው ተስተካክሎ ሪፖርት እየቀረበ ስለመሆኑ ቢሮው የሚያረጋግጥበት ስርዓት መዘርጋት እንዳለበት አስተያየት ተሰጥቶ ቢሮው ለየሴክተር መ/ቤቶች በዚሁ መሠረት የተስተካከለ ሪፖርታቸውን እዲያሳውቁ ደብዳቤ መጻፋንና ክትትልም እንደሚያደርግ በመግለጽ ምላሽ ሰጥቷል፡፡

**የተከበሩ አፈ-ጉባዔ!**

**የተከበሩ ፕሬዚደንት!**

**የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

**መ/ቤታችን በ2006/2007 በጀት ዓመት ያከናወነውን የ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ውጤት ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡**

29. መ/ቤቱ በዚህ ሪፖርት ያካተተው ሒሳባቸው በ2006/2007 በጀት ዓመት ኦዲት የተደረጉ የ368 መ/ቤቶች የ2006 በጀት ዓመት የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ውጤት ነው፡፡ የ2006 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በአወቃቀር እርከን ሲታይ በክልል/ማእከል 165(45%)፣በዞን 3 (0.8%)፤በከተማ አስተዳደሮች 32 (8.6%) ቀሪዎች 168 (45.6%) በወረዳ ደረጃ ያሉ ናቸው፡፡

30. ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብትና ሰነዶች፣ የሂሳብ መግለጫዎች እንዲሁም በየደረጃው ያሉ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች የሠጧቸው ማብራሪያዎች ናቸው:: ከዚህም በተጨማሪ ከ3ኛ ወገኖች የተገኙ ብቃትና ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች ሥራ ላይ ውለዋል:: የመ/ቤቶቹን ሂሳብ ኦዲት ማድረግ የመ/ቤታችን ኃላፊነት ሲሆን የሂሣብ መግለጫዎች የማዘጋጀት፣ ኦዲት የማስደረግና የሥሩበትን ሁኔታ የማስረዳት እንዲሁም በኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ እርምጃ መውሰድ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኃላፊነት ነው:: ከኦዲት ስልት አንፃር ከ368 መ/ቤቶች ውስጥ 334 (90.8%) በንሞና እንዲሁም 34 (9.2%) መ/ቤቶች የልዩ ኦዲት ጥቆማ ቀርቦባቸው በዝርዝር ኦዲት የተደረጉ ናቸው፡፡

**የኦዲት አስተያየት፤**

31. የ2006 በጀት ዓመት ሒሳባቸው ኦዲት ከተደረጉ 368 መ/ቤቶች ውስጥ 34 መ/ቤቶች በልዩ ኦዲት የተደረጉ በመሆኑ የኦዲት አስተያየት አልተሰጠባቸውም፡፡ በመሆኑም የኦዲት አስተያየት ከተሰጠባቸው 334 መ/ቤቶች ውስጥ 323 (96.7%) **ከዚህ በስተቀር፤** ለ4 (1.2%) **አስተያየት መስጠት አለመቻል፤** ለ6 (1.8%) **አጥጋቢ አይደለም፤** ለ1 (0.3) **ንፁህ** የኦዲት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ በ2005 በጀት ዓመት ኦዲት ተደረጎ የተሰጠዉ የኦዲት አስተያየት በ2006 በጀት ዓመት ከተሰጠው የኦዲት አስተያየት ጋር ሲነጻጸር **"አስተያየት መስጠት አለመቻል"** እና **"አጥጋቢ አይደለም"** የሚለው በ3.4% መቀነሱ የሂሣብ አያያዝ ስርዓቱ እየተሻሻለ መምጣቱን የሚያመላክት ሲሆን አስተያየት የማይሰጥበት የልዩ ኦዲት ሂሣብ ደግሞ በ2.2% መጨመሩ ህብረተሰቡ የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር የመታገል ልምዱ እየጨመረ መሄዱን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል **"ከዚህ በስተቀር"** የሚለው አስተያየት ተቀራራቢ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

32. **"አስተያየት መስጠት አልተቻለም"** የሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው መ/ቤቶች መንግስት የመደበላቸውን ሀብት እንዴት ስራ ላይ እንዳዋሉት የሚገልፅ የተሟላ ማስረጃ ያልቀረበባቸው፣ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓታቸው ደካማ የሆነ እና የሒሳቡን ትክክለኛነት በኦዲት ማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ናቸው፡፡ ይህ የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው መ/ቤቶች አዲዓርቃይ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል፣ ጃዊ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት፣ ወልዲያ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ እና በየዳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ናቸው፡፡ በሌላ በኩል **"አጥጋቢ አይደለም"** የሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው መ/ቤቶች መንግስት የመደበላቸውን ሀብት በአግባቡና ህጉ በሚፈቅደው አሰራር መሰረት ስራ ላይ ያላዋሉና የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመባቸው መ/ቤቶች ናቸው፡፡ ይህ የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው መ/ቤቶች እነብሴ ሳር ምድር ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል፣ ቋራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል፣ ታች አርማጭሆ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል፣ ደንቢያ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል፣ ጃናሞራ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል እና ጠለምት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ናቸው፡፡ አስተያየት መስጠት አለመቻልና አጥጋቢ ያልሆነ የኦዲት አስተያየት የተሰጡባቸው መ/ቤቶች ግኝቶቻቸውና የአሰራር ችግሮቻቸው ጉልህና መሠረታዊ በመሆኑ ትኩረት ሰጥቶ ማረምና ተጠያቂነትን ማጠናከር የሚገባ ሆኖ ከአጠቃላይ ኦዲት ተደራጊዎች መካከል 324 (97%) መ/ቤቶች በሪፖርቱ ውስጥ ተለይተው ከተገለፁት ግኝቶች በስተቀር ግኝቶቹም ጉልህና መሰረታዊ ያልሆኑ እንዲሁም የሒሳብና የመንግስት ንብረት አስተዳደራቸው በአንጻራዊነት የተሻለ ሆኖ የታየባቸው መ/ቤቶች ናቸው፡፡

**የኦዲት ሪፖርቶች ምላሽ አሰጣጥ፤**

33. በበጀት ዓመቱ በመደበኛ ኦዲት ከተደረጉት 334 መ/ቤቶች 80 (23.9%) እና በልዩ ኦዲት ከተሰሩት 34 መ/ቤቶች 19 (55.8%) የሚሆኑት ምላሽ ያልሰጡ በመሆናቸው ከባለፈው በጀት ዓመት ጋርም ሲነፃፀር መሰረታዊ መሻሻል ያልታየበት ችግር በመሆኑ ትኩረት ሰጥቶ መፍታት ይገባል፡፡ ምላሽ ያልሰጡ መ/ቤቶችን ይህ አጭር ሪፖርት ከተወሰደበት ዝርዝር የዘገባ ሪፖርት ላይ መመልከት ይቻላል፡፡

**የጥሬ ገንዘብ ሒሳብ ኦዲት ውጤት፤**

34. የ2006 በጀት ዓመት ሒሳባቸው በመደበኛ ኦዲት ከተደረገ 334 መ/ቤቶች መካከል 98 (29.3%) መ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2006 ዓ.ም ላይ ያለውን የጥሬ ገንዘብ ሒሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ ይህ አሃዝ ቀላል ተደርጎ የሚወሰድ ባይሆንም ከ2005 በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር በወቅቱ በመደበኛነት ኦዲት ከተደረገ 142 መ/ቤቶች 59 (41.5%) የነበረ በመሆኑ በዚህ በጀት ዓመት አንፃራዊ መሻሻል ያለ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡

**የገቢ ሒሳብ ኦዲት ውጤት፤**

35. የገቢ ሒሳብ ኦዲት ስራችን ያልተሰበሰበ (ውዝፍ) ገቢንና ለኦዲት ሊቀርቡ የሚገባቸው የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞችን የሚመለከት ነው፡፡ መንግስት የበጀት ዓመቱን ስራ ለማከናዎን ዕቅድ የሚነድፈው ገቢ የመሰብሰብ ስልጣን የተሰጣቸው መ/ቤቶች የገቢ ግብር የህግ ማዕቀፎችን መሰረት

በማድረግ ገቢ ይሰበሰባል በሚል ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ኦዲት ተደራጊዎች በገቢ አሰባሰብ ሥርዓቱ ገቢ እየሰበሰቡ መሆኑ ኦዲት ሲደረግ በ43 መ/ቤቶች ብር 110,563,965.65 ውዝፍ ገቢ ተገኝቷል፡፡ ከብር 1 ሚሊዮን በላይ ከፍተኛ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ ከሚታይባቸው ዞኖች መካከል ኦሮሞ ብሄረሰብ አስተዳደር የከምሴ ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤት ብር 59,703,523.75 (54%)፣ ሰሜን ጐንደር ዞን ብር 37,953,632.53 (34.3%) (ከዚህ ውስጥ የጎንደር ከተማ አስተ/ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 32,162,567.32 ይይዛል)፤ ምስራቅ ጐጃም ብር 8,143,077.78 (ከዚህ ውስጥ የደብረ ማርቆስ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 6,946,654.54 ይይዛል)፣ ደቡብ ጎንደር ዞን አስተዳደር ብር 1,846,589.29 እና በአዊ ብሄረሰብ አስተዳደር የጃዊ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 1,710,550.49 ከፍተኛውን ትርሻ ይይዛሉ::

36. ይህ በዚህ እንዳለ ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ተሚልተው እንዲቀርቡ ተጠይቆ በ63 መ/ቤቶች ብር 15,646,753.49 የያዙ ደረሰኞች ለኦዲት መቅረብ ባለመቻላቸው የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ናቸው፡፡ ከብር 1 ሚሊዮን በላይ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዙት ጃዊ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 4,320,635.42፤ ፎገራ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 2,436,484.59፤ ስማዳ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት 1,280,241.00፤ ወግዲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,069,085.96 መጠን የያዙ የመሬት መጠቀሚያ ገቢ ግብር መሰብሰቢያና የስፖርት ምክር ቤት ገቢ ደረሰኞች ስለትክክለኛነታቸው በኦዲት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ ይህም ለኦዲት ባልቀረቡት ደረሰኞች ገቢው በታሪፉ መሠረት በትክክል ለመሰብሰቡና ገቢ ለመደረጉ ባለመረጋገጡ በጉዳዩ ላይ አስተያየት ለመስጠት ገደብ የተጣለና ጥርጣሬን ያሳደረ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

37. በሌላ በኩል የንግድ ትርፍ እና የስራ ገቢ ግብር በግብር አዋጅ፤ ደንብና መመሪያ መሰረት የዕቃና አገልግሎት ግዥ ክፍያ ሲፈጸምና ደመወዝ እንዲሁም የተለያዩ ክፍያዎች ሲፈፀሙ መ/ቤቶች ከተከፋይ ሒሳብ ላይ ቀንሰው እንዲሰበስቡ የሚጠበቅ ቢሆንም ከ73 መ/ቤቶች ብር 1,547,275.79 ሳይሰበሰብ የተገኘ ሲሆን በ6 መ/ቤቶች ደግሞ የገቢው ሕጋዊነትና የታሪፍ ትክክለኛነቱን የሚያስረዳ ማስረጃ ሳይሟላ ገቢ የመሰብሰብ አሰራር ተስተውሏል፡፡

**የወጪ ሒሳብ ኦዲት ውጤት፤**

**የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመባቸው የወጪ ሒሳቦች፤**

38. በ2006 በጀት ዓመት ሒሳባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች መካከል በ20 መ/ቤቶች ብር 14,483,471.30 የማጭበርበር ድርጊት ተፈፅሞበት ተገኝቷል፡፡ የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመባቸው ዘዴወች ጠቅለል ተብለው ሲታዩ ላልተሰራ ስራ ወይም ላልተገኘ አገልግሎት ክፍያ መፈፀም፤ የደመወዝ ወጪን በድጋሜና በብልጫ በማፅደቅ የመንግስትን ገንዘብ ለግለሰብ ጥቅም ማዋል፤ ሰነዶችን በመሰረዝና በመደለዝ፤ የመንግስትን የግዥ ስርዓት በመጣስ ባልተገባ ተጠቃሚነት ወጪን ለግለሰብ ጥቅም ማዋልና ሌሎች ተቀራራቢ አይነት ዘዴዎችን በመጠቀም የመንግስት ገንዘብ ለግለሰቦች ጥቅም እንዲውል

ማድረግን ያካትታል፡፡ የወጪ መጠናቸው ከብር 500,000.00 በላይ የሆነና ከፍተኛ የወጪ ማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመባቸው መ/ቤቶችም፤ የጠለምት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 8,998,222.57፤ በየዳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,519,571.08፤ የታች አርማጭሆ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 891,331.25፤ ባህር ዳር ከተማ ውሃ አገልግሎት ጽ/ቤት ብር 692,926.51 ናቸው፡፡ እርምጃ አወሳሰዱን በሚመለከት ሁሉንም የግኝት ሪፖርቶች ለሚመለከታቸው የፍትህ አካላት ማለትም ለፍትህ ቢሮና ለሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ያሳወቅን ሲሆን በግብረ-ምልሶቹም ህግን ለማስከበር እንቅስቃሴ ያለ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

**ለሚመለከተው አካል ፈሰስ ያልተደረገ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤**

39. በ22 መ/ቤቶች ለስራ ተቋራጮች የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 3,896,720.29 በትክክል ለሚመለከተዉ ገቢ ሠብሳቢ መ/ቤት ፈሠስ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብለት ተገኝቷል፡፡ገንዘቡ በወቅቱ ፈሠስ መደረጉን ክትትል ባለመደረጉ ታክሱ ከመንግስት ተቋማት ተሰብስቦ ለረዥም ጊዜ በሰብሳቢዎቹ እጅ እየተያዘ ለስራ ማስኬጃ የሚውልበትና ከጊዜ ብዛትም ፈሰስ የማይደረግበት ሁኔታ ከመኖሩም በላይ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ የተከፈለዉ ደግሞ ታክሱ ለመንግስት ገቢ እንዲደረግ የሚያስገድድ የመቆጣጠሪያ ስልት ስለማይኖረው ምን ጊዜም ሊሰበሰብ ስለማይችል አፈፃፀሙ የመግስትን ገንዘብ በማጭበርበር ከተጠቃሚው (ከከፋዩ) በመንግስት ስም ሰብስቦ ለግል ጥቅም በማዋል እንዲሁም በሌሎች ዜጎች ላይ ኢፍታዊ የገበያ ውድድር በመፍጠር በደል የሚደርስ በመሆኑ ላለፈው ትኩረት በመስጠት እንዲሰበሰብ ለወደፊቱም በክልል ደረጃ የተጀመረው የመንግስት ተቋማት ታክስን ቀንሶ የማስቀርት አሠራር እስከ ታችኛው አደረጃጀት ድረስ በማውረድ ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባ ሆኖ ይታያል፡፡

**ያለአግባብ የተፈፀመ ክፍያ፤**

40. ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈፀሙ ስለመሆናቸው ሲጣራ በ177 (48%) መ/ቤቶች የተለያየ ዕቃና አገልግሎት ወጪ ሲፈፀም በብልጫ እንዲሁም የመስክ ስራ ላላከናወኑ ሠራተኞች የተከፈለ የውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች በድምሩ ብር **22,779,307.76** አላግባብ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ ያለአግባብ ከተከፈለው ክፍያ ውስጥ ከብር 500,000.00 በላይ ድርሻ የሚይዙት መ/ቤቶች፤ የክልል ም/ቤት ጽ/ቤት ብር 8,595,494.94፤ የግብርና ቢሮ የ2005 የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ማስፈፀሚያ (MDG) በጀት ብር 1,556,607.92፤ ገጠር መንገዶች ባለስልጣን ብር 905,728.79፤ ውሃ ሐብት ልማት ቢሮ የ2005 እና የ2006 የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ማስፈፀሚያ (MDG) በጀት በድምሩ ብር 1,622,811.99፤ ጤና ጥበቃ ቢሮ የ2006 የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ማስፈፀሚያ (MDG) በጀት ብር 2,629,667.14፤ ዳህና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 653,897.50፤ ፋርጣ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 779,517.80 እና ደ/ታቦር ከተማ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል 600,781.85 ይገኙበታል፡፡ የ2006 በጀት ዓመት ያለአግባብ የተከፈለ ክፍያ ከ2005 በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር ምንም እንኳን

በመ/ቤት ቁጥር በ71 ብልጫ ቢኖረውም በገንዘብ መጠን ግን የመጨመር ዝንባሌ ያለው በመሆኑ ትኩረት የሚያስፈልገው ነው፡፡ በግብረ-መልሶች ለመከታተል እንደተሞከረውም ብር 1,240,440.86 የተተካ ሲሆን በቀሪው የገንዘብ መጠን ላይ ስለሚገኝበት ሁኔታ ዝርዝር ግብረ-መልስ በኦዲት ተደራጊዎች በኩል አልተላከም፡፡

**የግንባታ ስራዎች ወጪ ኦዲት ውጤት፤**

41. ማንኛውም የግንባታ ክፍያ በውሉና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት በባለሙያ እየተረጋገጠ መፈጸም ሲገባው የግንባታ ክፍያ መመሪያን ባልተከተለ መንገድ መጀመሪያ ከተያዘው የግንባታ ውል ጋር ባልተጣጣመ ሁኔታ በ39 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 21,662,955.93 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ ከዚህም ውስጥ በግኝት ከ1 ሚሊዮን ብር በላይ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት መ/ቤቶች ቴክኒክና ሙያ ኢንተር ፕራይዞች ልማት ቢሮ የ2005 የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ማስፈፀሚያ (MDG) በጀት ብር 3,411,737.99፣ ደ/ማርቆስ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 2,196,900.44፣ ሞጣ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 2,853,721.18፣ ጐንደር ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 4,221,414.29፣ ደ/ታቦር ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,230,469.12፣ ኤፍራታና ግድም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,189,869.82 የተገኘባቸው ናቸው፡፡

**ለኦዲት ያልቀረቡ የወጪ ማስረጃዎችን በሚመለከት፤**

42. ክፍያዎች በተገቢው ማስረጃ ተደግፈውና መ/ቤቱ ለተጠቀመበት ዕቃና አገልግሎት በትክክል ስለመዋላቸው በኦዲት ለማረጋገጥ ክፍያ የተፈጸመባቸው የወጪ ማስረጃዎች ተሟልተው ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ21 መ/ቤቶች ብር 32,397,874.07 የተገኘ ሲሆን ከብር 500,000.00 በላይ የተገኘባቸው መ/ቤቶችም ኮምቦልቻ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ብር 925,274.55፣ ደ/ማርቆስ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 859,291.03፣ አለፋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,919,285.03፣ ምስራቅ በለሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 2,076,500.00፣ ጐንደር ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 4,046,110.12፣ ደ/ታቦር ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 6,854,975.10፣ ዋድላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 3,024,123.77 ፣ ደሴ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 1,377,275.16 የያዙ ማስረጃዎቻቸው ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የወጪዎቹን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

**የግዥ ሥርዓትን ያልተከተለ የወጪ ሒሳብ፤**

43. የዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ አፈፃፀም በስራ ባለው የዕቃና አገልግሎት ግዥ መመሪያ መሠረት ስለፈፀሙ እንዲሁም የተሻለ የዕቃ ጥራትና ዋጋ ስለመገኘቱና የግዥ አፈፃፀም ሒደቶች የተሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ219 (59%) መ/ቤቶች ብር 95,503,044.41 ዋጋ ያላቸው ግዥዎች የግዥ ሥርዓቱ የሚጠይቀውን መሥፈርት ሳያሟሉ ተከናውነው ተገኝተዋል፡፡ በግኝቱ ከ2 ሚሊዮን ብር በላይ የታየባቸው መ/ቤቶችም ደ/ታቦር ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ብር 3,632,193.78፣ ፍኖተ ሠላም ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል የ2002 እና የ2004 በጀት ዓመት በድምሩ ብር 10,756,842.10 ፤

ደ/ማርቆስ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 5,161,377.29፣ ተንታ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 6,270,408.45 ናቸው፡፡ የ2006 በጀት ዓመት የግኘ ሒሳብ ኦዲት በ2005 በጀት ዓመት ኦዲት የ118 መ/ቤቶች ግኝት ከነበረው ብር 107,343,734.23 ጋር ሲነፃፀር በ2006 በመ/ቤት ቁጥር በ101 ብልጫ የነበረው ቢሆንም በገንዘብ መጠን ደግሞ በብር 11,840,689.82 ቀንሶ መታየቱ ኦዲት ተደራጊዎች የግኘ መመሪያውን ተከትለው ለመስራት ያላቸው ዝግጁነት መጠነኛ የሚባል ቢሆንም ጥሩ መሻሻል ያለ መሆኑን ያሳያል፡፡

**የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ኦዲት ውጤት፤**

44. የመንግስት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች በክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003 አንቀጽ 53 እና በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 02/2003 እና ተያያዥ የህግ ማዕቀፎች አግባብ ንብረቶች በአግባቡ ተመዝግበው፤ ክትትል እየተደረገባቸውና በየዓመቱ ቆጠራ እየተከናወነ የንብረት ሒሳቡም በመ/ቤታችን ኦዲት መደረግ ይኖርበታል፡፡ በዚሁ መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት 334 መ/ቤቶች መካከል በ117(35%) መ/ቤቶች የንብረት ኦዲት ማድረግ አልተቻለም፡፡ለዚህም ዋና ዋና ምክንያቶች በዝርዝር የዘገባ ሪፖርቱ ላይ ተመልክተዋል፡፡

**የተከበሩ አፈ-ጉባዔ!**

**የተከበሩ ፕሬዚደንት!**

**የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

**ከዚህ ቀጥሎ የማጠቃለያና የማሻሻያ አስተያየቶችን አቀርባለሁ፡፡**

**የማጠቃለያና የማሻሻያ አስተያየቶች፤**

**ማጠቃለያ**

**የመ/ቤታችን የ11 ወር ዕቅድ አፈፃፀም በሚመለከት፤**

45. የ2007 በጀት አመት የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ማጠቃለያ እንደመሆኑ መጠን አፈፃፀሙም ከግቦች አንፃር ሲታይ በቁልፍ ስትራቴጅው የኦዲት ሰራዊት ግንባታ ረገድ ከፍተኛ ርብርብ የተደረገ መሆኑና በቀጣይ ጊዚያት ሙሉ የሰራዊት ቁመና ያለው ሰራዊት ለመገንባት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮአል፡፡ ከኦዲት ሽፋን አንፃር በበጀት አመቱ የ368 መ/ቤቶችን ኦዲት በማድረግ የዕቅዱን ከ76.7% በላይ በመፈፀም አጠቃላይ ሽፋናችን 54% ማድረስ ተችሏል፡፡ ይህ አፈፃፀም ከዚህ በፊት ከነበሩ አፈፃፀሞች ሻል ያለ ይሁን እንጅ በቂ ተደርጎ የሚወሰድ ሽፋን አይደለም፡፡ በክዋኔ ኦዲት ረገድ አፈፃፀማችን 92% ነው፡፡ የ2005 የክልሉ መንግስት የተጠቃለለ ፈንድ ሒሳብ ኦዲት 100% የተጠናቀቀ ሲሆን የደንበኞች እርካታ ሁኔታም ከ90% በላይ በመሆኑ ጥሩ የሚባል ነው፡፡

**የኦዲት አስተያየትን በሚመለከት፤**

46. የ2006 በጀት ዓመት ሒሳባቸው በመደበኛነት ኦዲት ከተደረጉ 334 መ/ቤቶች ውስጥ 323 (96.7%) መ/ቤቶች **"ከዚህ በስተቀር"** የሚል ኦዲት አስተያየት ያገኙ በመሆኑ አብዛኞቹ የክልላችን መ/ቤቶች የክልሉን የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር መሰረት አድረገው በጀትን ለመምራት የተሻለ ዝግጁነት ያለ መሆኑን ያመላክታል፡፡ በሌላ በኩል ቁጥራቸው ጥቂት የሚባል ቢሆንም የፋይናንስና ንብረት አስተዳደራቸው የከፋ የሚባሉ መ/ቤቶችም አሉ፡፡ ንፁህ የኦዲት አስተያየት የሚሰጣቸው መ/ቤቶች ቁጥርም በጣም ትንሽ ነው፡፡

**ምላሽ አሰጣጥን በሚመለከት፤**

47. በበጀት ዓመቱ በመደበኛ ኦዲት ከተደረጉት 334 መ/ቤቶች 80 (23.9%) እና በልዩ ኦዲት ከተሰሩት 34 መ/ቤቶች 19 (55.8%) የሚሆኑት ምላሽ ያልሰጡ በመሆናቸው ከባለፈው በጀት ዓመት ጋርም ሲነፃፀር መሰረታዊ መሻሻል ያልታየበት ነው፡፡

**የጥሬ ገንዘብ ሒሳብ ኦዲትን በሚመለከት፤**

48. የ2006 በጀት ዓመት ሒሳባቸው በመደበኛ ኦዲት ከተደረጉት 334 መ/ቤቶች የ98 (29.3%) መ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2006 ዓ.ም ላይ ያለውን የጥሬ ገንዘብ ሒሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ናቸው፡፡

**የገቢ ሒሳብ ኦዲት ውጤትን በሚመለከት፤**

49. የ2006 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረገ 368 መ/ቤቶች ውስጥ በ43 መ/ቤቶች ብር 110,563,965.65 ባለው የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት መሠረት በወቅቱ ሳ□ሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ተሟልተው እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ63(16.9%) መ/ቤቶች ብር 15,646,753.49 የያዙ የገቢ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

**የወጪ ሒሳብ ኦዲትን በሚመለከት፤**

50. የ2006 በጀት ዓመት ሒሳባቸው ኦዲት ከተደረጉ በ19 መ/ቤቶች የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም መጠኑ ቀላል ያልሆነ ገንዘብ ለግል ጥቅም ውሏል፡፡ በኦዲት ተደራጊዎች በኩል በተፈጸሙ የዕቃና አገልግሎት ግዥዎች ክፍያ በተፈጸሙ ሂሳቦች ለሚመለከተዉ ፈሠስ ሳይደረግ የቀረ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ የተለያየ ዕቃና አገልግሎት ግዥዎች ወጪ ሲፈፀም ከተያያዘው ማስረጃ በላይ በብልጫ የተፈጸመ፣ የግንባታ ክፍያ በውሉና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት በባለሙያ እየተረጋገጠ መፈጸም ሲገባው የግንባታ ክፍያ መመሪያን ባልተከተለ መንገድ ከግንባታ ውል ጋር ባልተጣጣመ ሁኔታ፣ የተለያየ የዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈጸም ለተከፈለው ገንዘብ የወጪ ደረሰኝ ወይም ፋክቱር ሳይቀርብለት በወጪ ጸድቆ የተመዘገበ፣ የግዥ ሥርዓት የሚጠይቀውን መሥፈርት ሣያሟሉ የተከናወኑ ግዥዎች፣እንዲሁም የመስክ ስራ ላላከናወኑ ሠራተኞች የተከፈለ የውሎ አበል፣ ስራ ላይ ላልዋለ ነዳጅ በቀረቡ ሰነዶችና ሌሎች ምክንያቶች አላግባብ ክፍያዎች ተፈጽመው ተገኝተዋል፡፡ በሌላ በኩልም ክፍያዎች በተገቢው ማስረጃ ተደግፈውና መ/ቤቱ ለተጠቀመበት ዕቃና አገልግሎት በትክክል ስለመዋላቸው በኦዲት ለማረጋገጥ ክፍያ የተፈጸመባቸው የወጪ ማስረጃዎች ተሟልተው ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቀው ሳይቀርቡ የቀሩበት ሁኔታም ተስተውሏል፡፡ በመሆኑም ከጊዜ ወደ ጊዜ ውስብስብ በሆነ መልኩ እያጋጠመ ያለውን ብክነት በተጠናከረ የጸረ-ኪራይ ሰብሳቢነት ትግል በማገዝ የፋይናንስ ተጠያቂነትን ማጎልበት ይገባል፡፡

**የንብረት ሒሳብ ኦዲት ውጤትን በሚመለከት፤**

51. የመንግስት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች በክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003 አንቀጽ 53 እና በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 02/2003 እና ተያያዥ የህግ ማዕቀፎች መሠረት ንብረቶች በአግባቡ ተመዝግበው፣ ክትትል እየተደረገባቸውና በየዓመቱ ቆጠራ እየተከናወነ የንብረት

ሒሳቡም ለኦዲት ዝግጁ መደረግ እንዳለበት በተመለከተው መሰረት ይኸው በትክክል እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት 334 መ/ቤቶች መካከል በ117 (35%) መ/ቤቶች የንብረት ሂሳብን አመዛዝኖ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ኦዲት ማድረግ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ ኦዲት ማድረግ ያልተቻለባቸውን ምክንያቶች ይህ ሪፖርት ከተወሰደበት ዝርዝር ዘገባ መመልከት ይቻላል፡፡

**የተከበሩ አፈ-ጉባዔ!**

**የተከበሩ ፕሬዚደንት!**

**የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

**ከዚህ ቀጥሎ የማሻሻያ አስተያየቶችን አቀርባለሁ፡፡**

በዚህ በጀት ዓመት ባቀረብነው የመ/ቤታችን ዕቅድ አፈፃጸም ላይ የተስተዋሉ ውስንነቶች፣በኦዲት ተደራጊዎች የታዩ ግኝቶች ተሻሽለው የኦዲት ሽፋናችን እንዲያድግና የመንግስት መ/ቤቶች የፋይናንስና የንብረት አስተዳደርና አመራር ሥርዓት መጠናከር እንዲችል የሚከተሉትን የማሻሻያ አስተያቶችን አቀርባለሁ፡፡

**የመ/ቤታችን የ2007 የ11 ወር ዕቅድ አፈፃፀምን በሚመለከት፤**

**የክዋኔና አካባቢ ጥበቃ ኦዲት ልዩ ትኩረት የሚያስፈልገው ስለመሆኑ፤**

52. ባለፉት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታት ሰፊ ትኩረት የተሰጠው ለፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ስለነበር የክዋኔና አካባቢ ጥበቃ ኦዲት ትኩረት አናሳ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ይህንን በመገንዘብ በ2007 በጀት ዓመት የክዋኔና አካባቢ ጥበቃ ኦዲት ራሱን ችሎ በስራ ሒደት ደረጃ እንዲደራጅ የመሰረታዊ የስራ ሒደት ለውጥ ጥናት በማድረግ ለሚመለከተው የመንግስት አካል አቅርበን ነበር፡፡ይሁን እንጅ በበጀት አመቱ ጥናቱ ፀድቆ ባለመምጣቱ ወደ ስራ መግባት ስላልተቻለ ለ2008 በጀት አመት እና ቀጣይ ጊዜያት መ/ቤታችን ለክዋኔና አካባቢ ጥበቃ ኦዲት ልዩ ትኩረት መስጠት እንዲችል አደረጃጀቱ ጸድቆ ወደ ስራ ሊገባ ይገባል፡፡

**ልምድ ያላቸው ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው ባለሙያዎች ፍልሰት መፍትሄ የሚሻው መሆኑ፤**

53. በሐገራችን ከ2 ያልበለጡ ኮርሶችን የሚያካትቱ ተዛማጅ ሙያዎች በስተቀር በቀጥታ በኦዲት ሙያ የሚያስመርቅ ዩኒቨርሲቲ/ተቋም ካለመኖሩም በላይ የኦዲት ሙያ በባህሪው ከመደበኛ የትምህርት ዝግጅት በላይ በስራ ላይ ረዘም ላለ ጊዜ የተግባር ልምምድን የሚጠይቅ በመሆኑ ጥራት ያለው የኦዲት ስራ ለማከናወን በዘርፉ ልምድ ያላቸው ከፍተኛ ባለሙያዎች እጅግ አስፈላጊ ናቸው፡፡ ነገር ግን በዚህ የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የተሻለ ጥቅማ ጥቅም ፍለጋ ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ ከፍተኛ የሙያ ብቃትና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች በየአመቱ መ/ቤታችን ለቀዋል፡፡ ይህ ሁኔታ በኦዲት ጥራትና በእውቀት ሽግግር ላይ የሚያስከትለው ተፅዕኖ እጅግ አሳሳቢ ስለሆነ የመ/ቤቱን ባለሙያዎች ከክልሉ ሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ወጣ ብሎ በልዩ ሁኔታ በማስተናገድና የተለያዩ ማበረታቻዎች እንዲሰጡ በማድረግ ምክር ቤቱና የወከለው ህዝብ ከተቋሙ የሚፈለገውን ጥራት ያለው፣የጸረ ኪራይ ሰብሳቢነት ትግሉን የሚያግዝ፣ የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ገለልተኛ የሙያ

ምክርና ማስረጃ በመስጠት የሚጠበቅበትን አገልግሎት መስጠት እንዲችል ም/ቤቱም ሆነ ሌላ የሚመለከተው አካል በትኩረት ወስዶ አቅጣጫ ሊሰጥበት ይገባል፡፡

**የ2005 በጀት ዓመት የክልሉ መንግስት የተጠቃለለ ፈንድ ሒሳብ ኦዲትን በሚመለከት፤**

54. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የመደበኛ በጀት (የትሬዠሪ ሒሳብ) የባንክ ቁጥር ጂኦቪ-116 የባንክ ሒሳብ ማስታወቂያንና የባንክ ሌጀርን በየጊዜው ማስታረቅ፣ የተሰብሳቢና ተከፋይ ሒሳቦች ክምችት በፋይናንስ አስተዳደር መመሪያው መሰረት እልባት መስጠትን በሚመለከት ቢሮው ችግሩን ለመቅረፍ የጀመረውን እንቅስቃሴ በማጠናከር የማስተካከያ እርምጃዎች ዳር ሊደርሱ ይገባል፡፡

**የ2006 በጀት ዓመት ሒሳብ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ውጤትን በሚመለከት፤**

**የፋይናንስ ሪፖርት አቅራቢዎችና ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች አደረጃጀት መስተካከል የሚገባው ስለመሆኑ፤**

55. የክልላችን ልማት የፈጠራቸው አገልግሎት ሰጭ መ/ቤቶች ቁጥር በየጊዜው በመጨመሩና የክልል ሴክተር መ/ቤቶች ተጠሪ ተቋማት በተናጠል ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ተደርገው ስለሚወሰዱ ክልሉ ከሚመድበው በጀት አንፃርና የመ/ቤቶች ስፋት አኳያ የኦዲት ሽፋናችን አሁንም ዝቅተኛ የሚባል ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ ቀደምም በተደጋጋሚ ለተከበረው ም/ቤት እንዳቀረብነው በጀታቸውን የክልል ሴክተር መ/ቤት የሚይዝላቸው ተቋማት የሒሳብ እንቅስቃሴ ሪፖርታቸውን ተጠሪ ለሆኑለት ቢሮ ወይም ተቋም ወይም እንደአስፈላጊነቱ ለዞን ማዕከላት የሚልኩበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡ ከጉዳዩ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር መ/ቤታችን በ2008 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ማጠናቀቂያ ጊዜ ድረስ መድረኮችን በማመቻቸት አሰራሮችን መዘርጋት እንዲችል ም/ቤቱ ለሚመለከታቸው የክልሉ መ/ቤቶች አቅጣጫ ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡

**ኦዲት ተደራጊ ተቋማት የኦዲት አስተያየታቸው እንዲሻሻል ትኩረት መስጠት የሚገባቸው መሆኑ፤**

56. የኦዲት ተደራጊ ተቋማት የኦዲት አስተያየት መሻሻል ማሳየት የሚችለው በአጠቃላይ የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ስርዓታችን ላይ በሚደረጉ ማሻሻያዎችና በሚገኙ ውጤቶች ቢሆንም ከክልል እስከ ወረዳ ያሉ ኦዲት ተደራጊ ተቋማት የተዘረጋውን የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ስርዓት በጥብቅ ዲሲፕሊን በመፈጸም ነቀፌታ የሌለው የኦዲት አስተያየት (ንፁህ የኦዲት አስተያየት) ማግኘት እንዲችሉ አቅደው መስራት ይገባቸዋል፡፡

**በኦዲት ስራ አመራር ሪፖርት መልስ አሰጣጥና እርምጃ አወሳሰድ ረገድ የሚስተዋለው ችግር ሙሉ በሙሉ መቀረፍ የሚገባው ስለመሆኑ፤**

57. በዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 186/2003 አንቀፅ 21(3) መሰረት ከኦዲት ተደራጊ ተቋማት ግዴታዎች መካከል በሁሉም ኦዲት ተደራጊዎች መፈፀም የሚገባው በሪፖርቶች ላይ የተገለፁ ግኝቶችን አስመልክቶ በ15 ቀን ውስጥ ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድና ይሄንኑ ለዋና ኦዲተር መ/ቤት ማሳወቅ ነው፡፡ ይሁን እንጅ ይሄንኑ ድንጋጌ ወደ ጎን በመተው በግኝቶች ላይ ም/ቤቱ በእርምጃ

አወሳሰድ ማስረጃዎች ላይ ተመስርቶ በጥልቀት ከመምከርና አቅጣጫ ከማስቀመጥ አንፃር ገደብ በሚጥል መልኩ ምላሽ የማይሰጡ መ/ቤቶች ከመኖራቸውም በላይ እርምጃ አወሳሰዱም አዝጋሚ ስለሆነ ይህን በማያደርጉ ላይ መ/ቤታችን ከፍትህ አካላት ጋር በመሆን በቀጣይ ወደ ተጠያቂነት ከመሄዱ በፊት ኦዲት ተደራጊዎች ሙሉ በሙሉ ከዚህ ችግር የሚወጡበትን አሰራርና አካሄድ ቀርፀው ተግባራዊ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

**የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝ ስርዓት ላይ ቁጥጥርን ማጠናከር በሚመለከት፤**

58. ከግኝቶች መረዳት እንደሚቻለው በዘመኑ ኦዲት ከተደረጉት 334 መ/ቤቶች ውስጥ 29.3% በሚሆኑት ላይ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ በተለያዩ ምክንያቶች ማመዛዘን ያልተቻለ ሲሆን ይህም የህዝብና የመንግስትን ገንዘብ ለብክነትና የተለያዩ ምዝበራዎች የሚያጋልጥ በመሆኑ የተመደበ ሃብትን በሚገባ ይዞ ለኦዲት ዝግጁ አለማድረግ በራሱ ተጠያቂነትን የሚያስከትል መሆኑ ታውቆ በየተቋማቱ የሚገኙ ሥራ አመራሮችና የውስጥ ኦዲተሮች ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው ከችግሩ ሊወጡ ይገባል፡፡

**የገቢና የወጪ ሂሳብ ማጭበርበሪያ ክፍተቶችን ማጥበብ የሚችል የአሰራር ስርዓት ዘርግቶ በየጊዜው ማሻሻልና በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲፈጸም ማድረግ የሚያስፈልግ ስለመሆኑ፤**

59. በሪፖርታችን ላይ በግልፅ እንደተመላከተው በገቢና ወጪ ሂሳቦች ላይ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የመንግስትን ገንዘብ ለግል ጥቅም የማዋል ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ መልኩን እየቀየረ አብሮን ያለ ጉዳይ ነው፡፡ ከአጠቃላይ ስራ አንፃር በረጅም ጊዜ የፖለቲካል ኢኮኖሚ ለውጥ የሚፈቱ ችግሮች ቢሆኑም ጎን ለጎን ደግሞ ክፍተት የፈጠሩ አሰራሮችን እየፈተሹ በማስተካከል፤ የአመራሩንና የፈፃሚውን አቅም በመገንባት የመንግስትን ሃብት በአግባቡ ይዞ መጠቀም እንዲቻል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የፍትህ አካላትም የጀመሩትን ከኦዲት ተቋሙ ጋር በቅንጅት የመስራት አሰራር ይበልጥ በማጎልበት አጥፊዎች ላይ አስተማሪ የሆነ እርምጃ ሊወስዱና የፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት በሁሉም ዘንድ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

**የቋሚና አላቂ ዕቃዎች አያያዝና አጠባበቅ መጠናከር የሚገባው ስለመሆኑ፤**

60. በበጀት ዓመቱ በ117 (35%) መ/ቤቶች የቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ ተቋቁሞ የማይሰራባቸውና በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ ቆጠራ የማይከናዎን በመሆኑ የንብረት አያያዝና አጠባበቅን ኦዲት አድርጎ አስተያየት መስጠት ያልተቻለ ስለሆነ መ/ቤቶቹ ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ በማቋቋምና በየጊዜው ቆጠራ እያከናወነ ከመዝገቡ ከወጪ ቀሪ ጋር እያመሳከሩ ልዩነት ሲፈጠርም ተገቢውን ማስተካከያ እርምጃ እየወሰዱ ሊሰሩ ይገባል፡፡ የንብረት ሂሳብን በሚገባ እየተከታተሉ ለኦዲት ዝግጁ በማያደርጉ ላይ የምክር ቤቱ የየዘርፉ ቋሚ ኮሚቴዎችና የሚመለከታቸው የፍትህ አካላት ስራንና ሃላፊነትን በሚገባ ባለመወጣትና ሃብትን ባልተመቸ አመራር በመምራት ተጠያቂ የሚደረጉበትን አሠራርና የክትትል ስርዓት በመዘርጋት በችግሩ ላይ ለውጥ እንዲመጣ ጥረት ሊያደረጉ ይገባል፡፡

**በየደረጃው የሚገኙ የህዝብ ምክር ቤቶች በኦዲት ሪፖርት ላይ ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፤**

61. በየደረጃው የሚገኙ ም/ቤቶች ለየአካባቢያቸው በሚደርሰው የውጭ እና የውስጥ ኦዲት ሪፖርቶች በክልሉ ም/ቤት እንደሚደረገው ሁሉ በተለያዩ የም/ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች (በተለይም በበጀትና የመንግስት ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ) አማካኝነት ለየም/ቤቱ ጉባዔ በአጀንዳነት ቀርቦ ውይይት ሊደረግበትና አቅጣጫ እየተሰጠበት ክትትሉ ሊጠናከር ይገባል እንላለን፡፡

በመጨረሻም ይህ ጉባዔ የክልላችን ም/ቤት 4ኛ ዙር 5ኛ ዓመት የምክር ቤት ዘመን የማጠናቀቂያ ጉባዔ እንደመሆኑ መጠን ባለፉት 5 ዓመታት የምክር ቤቱ አፈ-ጉባዔዎች፣ የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች፣ የምክር ቤቱ አባላት ለስራችን መሳካትና ለክልላችን የፋይናንስ ግልፀኝነትና ተጠያቂነት መጠናከር ላደረጋችሁት የላቀ አስተዋፅኦ የከበረ ምስጋና በመ/ቤታችን ስም አቀርባለሁ፡፡ ለ5ኛ ዙር የሚደራጀው የክልላችን ም/ቤትም በተመሳሳይ መልኩ ለዋና ኦዲተር መ/ቤታችን የላቀ ድጋፍና እገዛ እንደሚያደርግም ሙሉ እምነት አለኝ፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ሁሉም ኦዲት ተደራጊዎችና የፍትህ አካላት ላደረጋችሁት የስራ ትብበር፣ የመ/ቤታችን የስራ ኃላፊዎችና ኦዲተሮች እንዲሁም አስተዳደር ሰራተኞች በዚህ ሪፖረት ለተገኙ ውጤቶችና ላሳያችሁት ታታሪነትና መልካም ስነ-ምግባር ከፍተኛ ምስጋናየን እያቀረብኩ፣ ባለፉት አምስት ዓመታት ለም/ቤት የምናቀርባቸው የኦዲት ሪፖርቶችን ህዝባችን በቀጥታ በቴሌቪዥንና ራዲዮ ፕሮግራሞች መከታተል እንዲችል የክልላችን ብዙሃን መገናኛ ድርጅት ላበረከተው አስተዋፅኦ ምስጋናየን እያቀረብኩ ሪፖርቴን በዚሁ አጠቃልላለሁ፡፡ አመሰግናለሁ!!

ደሴ ጥላሁን አያሌው

ዋና ኦዲተር

ሐምሌ/2007 ዓ.ም

ባህር ዳር!!